መልእክት አንድ

**ለኢያሱ የእግዚአብሔር ትእዛዝ፣ ተስፋ እና ማበረታታት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ኢያ. 1፡1-9

## I. ኢያሱ በሚከተሉት ገጽታዎች የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡-

ሀ. *ኢያሱ* የሚለው የዕብራይስጥ ስም የግሪኩ አቻው *ኢየሱስ* ነው (ዕብ. 4፡8፤ ሐዋ. 7፡45)፣ ይህም "ያሕዌ አዳኙ" ወይም "የያሕዌ ማዳን" (ማቴ. 1፡21፤ ዘኍ. 13፡16) ማለት ነው፡-

1. ፍጹም ሰላማችን እና ሙሉ እርካታችን በሆነው ክርስቶስ እኛን ወደ ክብር እና በእግዚአብሔር-ቃል ወደ ተገባው ምድር እረፍት ለመምራት (ዕብ. 2፡10፤ 4፡11፤ ዘዳ. 12፡9፤ ማቴ. 11፡28-30) *መሪያችን* የሆነው ክርስቶስ እንደ የመዳናችን መሪ እውነተኛው ኢያሱአችን ነው (ዕብ. 2፡10፤ 4፡8)።
2. ኢያሱ በሙሴ የተመለከተው ሕግን ክርስቶስ እንደ ጸጋ መተካቱን ያሳያል (ኢያ. 1፡2፤ ዮሐ. 1፡17)፤ ኢያሱ ሕዝቡን ወደ መልካሚቱ ምድር ለማስገባት የመጣው ሕግ ሰጪው ሙሴ ሲሞት ነው (ኢያ. 1፡1-4)፤ ኢያሱ እረፍታችን፣ የመልካሚቱ ምድር እውነታ የሆነውን ጌታ ኢየሱስን ወደ መደሰት ውስጥ የሚያመጣን መሪያችን የሆነውን ጌታ ኢየሱስን በምሳሌ ያሳያል (ዘዳ. 8፡7-10፤ 12፡9፤ ፊልጵ. 1፡19፤ ኤፌ. 3፡8፤ ቆላ. 1፡12፤ 2፡6-7፤ ዕብ. 4፡8-9፤ ማቴ. 11፡28-29)።

ለ. ከአማሌቅ ጋር በነበረው ጦርነት (ዘጸ. 17፡8-16)፣ አማሌቅ እንደ ወደቀው አሮጌው ሰው ጥቅል-ድምር ሥጋን በምሳሌ ያሳያል፤ ኢያሱ ከሥጋ ጋር የሚዋጋውና የሚገድለው ማንነት እንደሆነው በውስጥ እንደሚያድረው፣ እንደተዋጊው መንፈስ የአሁኑን እና ተግባራዊውን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል (ሮሜ 8፡9-13፤ ገላ. 5፡16-17፤ 24)፡-

1. የሥጋ አላማ መልካሚቱ ምድር ወደሆነው ሁሉን-ወዳካተተው ክርስቶስ ሙሉ ድሰታ ውስጥ እንዳንገባ ማስቀረት ነው።
2. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ በሦስታንዱ አምላክ ብልጥግናዎች በረከት ውስጥ መሳተፍ እንችል ዘንድ ከሥጋ ወደ መንፈስ አርነት ያወጣናል—ሮሜ 7፡17—8፡2፤ ገላ. 3፡14፤ ኤፌ. 1፡3-14።

ሐ. ከአሥራ ሁለቱ ሰላዮች እንደ ሁለቱ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ እምነታቸው በመውሰድ በእምነት የተሞሉ ልቦች ያላቸው ሰዎች በመሆን  የእግዚአብሔር ሕዝብ መልካሚቱን ምድር የራሳቸው ያደርጉ ዘንድ ለሆነው የእግዚአብሔር ፍላጎት ለመኖር፣ ኢያሱ በአርባ ዓመቱ ካሌብን ተቀላቀለ፤ በምድረ በዳ ከነበሩት በእግዚአብሔር ከተዋጁት መካከል ሁለት ድል-ነሺዎች፣ ኢያሱ እና ካሌብ ብቻ የመልካሚቱን ምድር ሽልማት ተቀበሉ—ዘኍ. 13፡30፤ 14፡6-9፣ 27-30፤ ሮሜ 10፡17፤ ገላ. 3፡3፣ 5፤ ዕብ. 11፡5-6፤ ፊልጵ. 3፡13-14፤ ተዛ. ሐዋ. 6፡5

1. በዘኍልቁ 13 እና 14 ባለው ዘገባ መሠረት፣ የእስራኤል ሕዝብ የማያምን ክፉ ልብ ነበራቸው፤ ኢያሱ እና ካሌብ ሕዝቡን "በእግዚአብሔር ላይ አታምፁ" (ቁ. 9) በማለት አጥብቀው አሳሰቧቸው አስጠነቀቋቸውም፤ እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት በጌታ አለማመን በእርሱ ላይ ማመጽ እንደሆነ ነው—ዘኁ 13፡31-33፤ 14፡1-3፣ 6-11፤ ዘዳ. 1፡26፣ 32።
2. ክርስቶስን እንደ መልካሚቱ ምድር ሙሉ በሙሉ ልንወርሰው ከሆነ፣ የማያምን ክፉ ልብ ያለው ከመሆን እንዲያድነን ጌታን መጠየቅ አለብን፤ እንዲህ ያለ የደነደነ ልብ ያለው መሆን ሕያው ከሆነው አምላክ መውደቅ፣ መዞር ነው—ቁ. 25-26፣ 28፣ 35-39፤ 9፡23፤ ሐዋ. 6፡5፤ ዕብ. 3፡7-13።
3. የክርስትና ምልልሳችን በእምነት እንጂ በማየት አይደለም (2 ቆሮ. 5፡7)፤ ስለዚህ፣ የእምነታችን ጀማሪ እና ፈጻሚ የሆነውን ኢየሱስን ያለማቋረጥ መመልከት አለብን (ዕብ. 12፡1-2)፤ እምነታችን ከራሳችን ሳይሆን ለእኛ ሊያምንልን ራሱን እንደ የሚያምነው ንጥረ-ነገር ከሚያካፍለው ከእርሱ ነው (ገላ. 2፡20፤ 2 ጴጥ. 1፡1)።
4. አለማመን ለክርስቲያን ታላቁ ኃጢአት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል፤ የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀን ከያዝን እና ካመንን፣ ሁሉ ደህና ይሆናል፤ በስሜቶቻችን ስንኖር እና ለእኛ የተሰጠ ቃል ኪዳኑ፣ ኑዛዜው በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ባሉት መለኮታዊ ሃቆች ለማመን የእምነት መንፈሳችንን ሳናንቀሳቅስ እና ልባችንን ወደ ጌታ ሳናዞር ስንቀር፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ እያመጽን፣ እግዚአብሔርን እየተሳደብን እና እርሱን ውሸታም እያደረግነው ነው—ዘዳ. 1፡25-26፤ ዕብ. 3፡12፤ 16-19፤ 4፡2፣ 6፤ 11፡1፤ ሮሜ 3፡4።
5. በወቀሳዎቻችን፣ በስሜቶቻችን እና በከባቢ ሁኔታዎቻችን ደመናዎች መስጋት ወይም መፍራት የለብንም፤ በአዲሱ ኪዳን ሥር መኖር እንጂ በማንኛውም ውድቀት፣ ድካም፣ ጨለማ ወይም አሉታዊ ነገር ማመን የለብንም፤ ቃል

ኪዳን የተገባልን ሕዝብ ነን፣ እያንዳንዱን ሁኔታ የሚመጥን የተስፋ ቃል ጥቅስ አለን—ዘፍ. 9፥8-17፤ ራእ. 4፥2-3፤ ሰቆ. 3፥22-23፤ ሮሜ 8፥1፤ 2 ቆሮ. 12፥9፤ 2 ጢሞ. 1፥10፤ 2፥1፤ ይሁዳ 24፤ 1 ዮሐ. 1፥9፤ 1 ቆሮ. 1፥9።

6. መንፈሳችን የአዲሱ ኪዳን የውርስ ኑዛዜዎች ሁሉ እውነታ የሆነው ከሞት የተነሣው፣ የእስትንፋሳዊው ክርስቶስ "የባንክ ሂሳብ" ነው፤ በሕይወት መንፈስ ሕግ እነዚህ ሁሉ ወደ ውስጣችን ይታደላሉ ለእኛም እውን ይሆናሉ፤ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሰዎች በቃል ኪዳኑ ሥር ያሉ ሰዎች ስለሆኑ፣ የቃል ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተብለን መጠራት እንችላለን—ኢሳ. 42፥6፤ 49፥8፤ ሮሜ 8፥2፣ 10፣ 6፣ 11፣ 16፤ ዕብ. 8፥10፤ ዮሐ. 16፥13።

**II. "በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም፤ ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ አልጥልህም፥ አልተውህም። ለአባቶቻቸው፡- እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና ጽና፥ አይዞህ። ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል"—ኢያ. 1፥5-7፡-**

ሀ. ኢያሱ ከሙሴ ጋር በነበረ ጊዜ ያሕዌ ከኢያሱ ጋር አብሮ እንደሚሆን መንገሩ ታላቅ ነገር ነበር፤ የሆነ ጊዜ ጌታ ለሙሴ "ህልዎቴ ከአንተ ጋር ይሄዳል፥ እረፍትም እሰጥሃለሁ" ብሎታል (ዘጸ. 33፥14 አ.መ.ት.)፤ ሙሴ ለእግዚአብሔር ልብ በጣም የቀረበ እና በእግዚአብሔር ልብ መሠረት የሆነ ሰው ስለነበር፣ የእግዚአብሔር መገኘት ሙሉ በሆነ መጠን ነበረው።

ለ. በአዲስ ኪዳን የኢየሱስ መገኘት አማኑኤል ነው፣ ትርጓሜውም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ማለት ነው (ማቴ. 1፥23፤ 18፥20፤ 28፥20)፤ ክርስቶስ እንደ የእውነታ መንፈስ፣ ሕይወት-እንደሚሰጠው መንፈስ አማኑኤል፣ በመንፈሳችን ውስጥ ያለው የመለኮታዊው ሥላሴ መገኘት ነው (2 ጢሞ. 4፥22)።

ሐ. በሚቀጥለው ዘመንና ለዘላለም ድንቅ የሆነው ክርስቶስ ሙሉ እና ዘላለማዊ ርስት ናሙና እንደሆነው እንደ ርስታችን መያዣ ዛሬ በመልካሚቱ ምድር የተመለከተውን ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ ለመደሰት ጽኑ እና በጣም ብርቱ ለመሆን የእምነት መንፈሳችንን ያለማቋረጥ ማንቀሳቀስ አለብን—2 ቆሮ. 4፥13፤ ኤፌ. 1፥14፣ 18፤ 2 ቆሮ. 1፥22፤ 5፥5-6።

መ. በማንኛውም ሁኔታ ክርስቶስን ለማጉላት፣ ይህም እርሱን ከፍ ባለ ድሰታ ለመለማመድ፣ ጌታን እንደ ጽናታችን እና ብርታታችን መውሰድ አለብን (ፊልጵ. 1፥20፤ 4፥11-13)፤ "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤ የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤ የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?" በማለት ሁልጊዜ ማወጅ እንችላለን—መዝ. 27፥1።

ሠ. ሞት በአንድ ወቅት ነግሦብን ነበር (ሮሜ 5፥14)፣ እኛም ሞትን ያለማቋረጥ በመፍራት በእርሱ ባርነት ሥር ነበርን፤ ጌታ ዲያቢሎስን ስለደመሰሰው እና ሞትን ስለሻረው (ዕብ. 2፥14-15፤ 2 ጢሞ. 1፥10)፣ አሁን የሞት ፍርሃት የለብንም፣ በእርሱ ባርነት ሥር ከመሆንም ተፈትተናል።

ረ. "እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥልምና፥ ርስቱንም አይተውምና" (መዝ. 94፥14)፤ "ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል?" (ዕብ. 13፥6)፤ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" (ሮሜ 8፥31)።

ሰ. የፍርሃት ሳይሆን የኃይል፣ የፍቅር እና ራስን የመግዛት መንፈስ የሆነውን በእግዚአብሔር-የተሰጠንን መንፈስ የምናቀጣጥል ሰዎች መሆን ያስፈልገናል (2 ጢሞ. 1፥6-7)፤ ስሜቶቻችን ሙሉ በሙሉ ውሸት ናቸው፤ ጠንካራ እንደሆንን፣ በፍቅር የተሞላን እንደሆንን እና በጣም ግልጽ እንደሆንን ሁልጊዜ ማመን እና ማወጅ አለብን፤ ያኔ እንደ መልካሚቱ ምድር እውነታ ሁሉን-ወዳካተተው ክርስቶስ ውስጥ ለመግባት እና ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ ለመደሰት መጽናት እና መበርታት እንችላለን (ኢያ. 1፥6)።

ሸ. በሁሉም መንገድ እርሱን ደስ ለማሰኘት ለጌታ እንደሚገባ በመመላለስ (ቆላ. 1፥10) በምንሄድበት ሁሉ ይከናወንልን ዘንድ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ሰማያዊ ራእይን ከሚመለከተው ከቅዱስ ቃሉ "ወደ ቀኝም ወደ ግራም" ማለት የለብንም (ቁ. 7)፤ ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር እንደሆነ እና እኛ እንዳልሆንን ያለማቋረጥ በማመን፣ ከመወሰዳችን በፊት "እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘን" ምስክርነት ማግኘት እንችላለን (ዕብ. 11፥5-6፤ ዘፍ. 5፥21-24)።

**III. "የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም። በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ አትፍራ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?"—ኢያ. 1፥8-9፡-**

ሀ. ኢያሱ በእግዚአብሔር ቃል መያዝ እና ቃሉ እንዲይዘው መፍቀድ ነበረበት (ተዛ. ቆላ. 3፥16)፤ በእግዚአብሔር ቃል በመያዝ እና በመሞላት በእግዚአብሔር ቃል የተገባውን ምድር በመውሰዱ ውስጥ መከናወን እና ስኬት ይኖረው ነበር።

ለ. ኢያሱ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጻፈውን ሁሉ የማከናወኑ ቁልፉ እና በእግዚአብሔር ቃል የተገባውን ምድር በመውሰዱ ውስጥ ላለው መከናወኑ፣ ስኬቱ፣ ጽናቱ እና ብርታቱ ቁልፉ የእግዚአብሔርን ቃል በቀንና በሌሊት በማሰላሰል ከአፉ እንዲለይ አለመፍቀዱ ናቸው፤ *አፍህ* የሚለው ቃል ማሰላሰል ተግባራዊ ልምምድ ላይ የሚውለው በዋናነት ጮክ ብሎ በመናገር እንደሆነ ያሳያል፡-

1. *ማሰላሰል* ለሚለው የዕብራይስጥ ቃል በትርጓሜው የበለጠ ነው፤ አምልኮን፣ ከራስ ጋር መነጋገርን እና ጮክ ብሎ መናገርን ያመለክታል፤ ቃሉን ማሰላሰል፣ ቃሉን በጥንቃቄ በማሰብ መቅመስ እና መደሰት ነው—መዝ. 119፡15፣ 23፣ 48፣ 78፣ 97-100፣ 148፣ ተዛ. ቁ. 9-11።
2. ጸሎት፣ ለራስ መናገር እና ጌታን ማወደስ ቃሉን በማሰላሰል ውስጥ መካተት ይችላሉ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ማሰላሰል ቃሉን እንደ የእርሱ እስትንፋስ መደሰት (2 ጢሞ. 3፡16) ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር መሰረጽ፣ እግዚአብሔርን ወደ ውስጥ መተንፈስ እና መንፈሳዊ ምግብን መቀበል ነው።
3. ቃሉን ማሰላሰል ላሞች ሣር እንደሚበሉ "ማመሰኳት" ነው (ዘሌ. 11፡3)፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስናሰላስል፣ ብዙ ጥንቃቄ በተሞላበት ማሰብ እና እንደገና በማሰብ እንቀበለዋለን፤ ላም ምንዣጊውን እንደሚያመነዥግ እንዲሁ፣ እኛም ከእግዚአብሔር ቃል የምንቀበለውን ነገር እንደገና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ በማሰብ ምግብ እንቀበል ዘንድ በማለዳ ቃሉን እየጸለይን-ስናነብ ሳለን ይህን ማድረግ እንችላለን።

ሐ. መዝሙረኛው "ትእዛዝህን አሰላስላለሁ፥ መንገድህንም እፈልጋለሁ። በትእዛዝህ ደስ ይለኛል፤ ቃልህንም አልረሳም" ብሏል—መዝ. 119፡15-16፡-

1. መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ቃል ሲያሰላስል፣ የደስታው ምንጭ፣ ደስታው እና ሐሴቱ ሆነው (ኤር. 15፡16)፣ የእግዚአብሔርንም ቃል አይረሳም፤ ስለዚህ፣ የማያቋርጥ እና ዘላለማዊ ምግብ ሆነለት (መዝ. 119፡105፣ 130)።
2. የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል፣ ቃሉን እናስታውሰዋለን በእርሱም ሕያዋን እንሆናለን—"ለባሪያህ ተስፋ ያስደረግኸውን ቃልህን አስብ። ቃልህ ሕያው አድርጎኛልና ይህች በመከራዬ ደስ አሰኘችኝ"—ቁ. 49-50።

መ. ቃሉን ማሰላሰል እየጸለዩ-ከማንበብ የበለጠ ብልጡግ፣ ሰፊ እና አካታች ነው፣ ምክንያቱም ጸሎትን፣ አምልኮን፣ ድሰታን፣ መነጋገርን፣ መስገድን እና የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል እጃችንን ማንሣትን እንኳን ሳይቀር ያካትታል (ቁ. 48)፤ ወደ እግዚአብሔር ቃል እጃችንን ማንሣት በሞቀ ስሜት እና በደስታ እንደምንቀበለው እና አሜን እንደምንለው ያመለክታል (ነህ. 8፡5-6)።

ሠ. በዚህ መንገድ የጌታን ቃል በመንፈሳችን ስንነካ እና ከእርሱ ጋር በማያቋርጥ ኅብረት ውስጥ ስንቆይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የመታጠብ፣ የመሞቅ፣ ትኩስ የመሆን፣ የመረስረስ እና አቅርቦት የማግኘት ስሜት ሊኖረን ይገባል፤ ማድረግ ያለብን አንዱ ነገር፣ ምርጡ ነገር እርሱን መንካት፣ እርሱን ማምለክ፣ በእርሱ ማመን፣ እርሱን መምጠጥ፣ እርሱን መደሰት፣ እርሱን መከታተል እና እርሱን ማትረፍ ነው—መዝ. 27፡4፤ ፊልጵ. 3፡8፣ 14።

ረ. የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰላሰል የእውነት ጊዜ ስንወስድ፣ በእግዚአብሔር ለመፋም እና እግዚአብሔርን ለማንጸባረቅ እየተሰረጽን ነው (2 ቆሮ. 3፡15-18)፤ "እንጸልይ ከየሱስ ጋር ኅብረት ለማድረግ፣ በገጽታው እየታጠብን፣ ተጥለቅልቀን በውበቱ፣ ልዕልናውን እናንጸባርቅ" ብለን የምንዘምረው ለዚህ ነው (*ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ መዝሙር* #784፣ 6ኛው የግጥም ስንኞች)።

ሰ. ጌታችን እና አምላካችን ሁሉን-እንዳካተተው ምድር እውነታ ወደ እርሱ ውስጥ እንድንገባና እንድንደሰተው ስላዘዘን፣ ለመጽናት፣ ለመበርታት እና ላለመፍራት ወይም ላለመደንገጥ ቃሉን አሜን ማለት አለብን፣ ምክንያቱም እስከዚህ ዘመን ፍጻሜ፣ እስከ መምጣቱ ጊዜ ድረስ አሕዛብ የመንግሥቱ ሰዎች እንዲሆኑ ደቀ መዛሙርት ስናደርጋቸው ሳለን በምንሄድበት ሁሉ አምላካችን ያሕዌ ከእኛ ጋር ነውና—ኢያ. 1፡9፤ ማቴ. 28፡20።

*© 2021 Living Stream Ministry*